አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች
የልዩ ትመህርት ቢሮ
2110 Washington Blvd. 2nd Floor
Arlington, Virginia 22204
703-228-6040

## ገለልተኛ የሆኑ ትምህርታዊ ምዘናዎች

“ገለልተኛ የሆነ ትምህርታዊ ምዘና” (IEE) ማለት ለተማሪው ትምህርት ኃላፊነት ባለው የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ተቀጣሪ ባልሆነ ብቃት ባለው ፈተና ሰጪ የሚካሄድ ምዘና ነው። አንድ ወላጅ የልጁን IEE የማግኘት መብት ያለው ሲሆን እንዲሁም IEE የት ማግኘት እንደሚቻል ጥያቄ በሚቀርብ ጊዜ የት ሊገኝ እንደሚችል መረጃ ሊሰጠው ይችላል።

እነዚህን መመሪያዎች ካነበቡና ምዘናዎን ካካሄዱ በኋላ ጥያቄዎች የሚኖርዎ ከሆነ እባክዎን የልዩ ትምህርት የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ዳይሬክተር ወይም የልዩ ትምህርት ተገዢነት ልዩ ባለሙያን በስልክ ቁጥር 703-228-6040 ያግኙ።

በልጅዎ የምዘና ሂደት ወቅት በተሰጠው ፈተና የማይስማሙ ከሆነ IEE ማግኘት የሚቻል ይሆናል። IEE የሚጠየቅ ከሆነ እባክዎ የሚከተለውን ያስተውሉ፡

1. ምዘናው እንዲካሄድ ሌላ የAPS ምዘና አድራጊ የመጠየቅ መብት አልዎት።
2. ለትምህርት ክፍሉ በመስራት ላይ የማይገኝ ብቃት ባለው ሰው የሚካሄድ ራሱን የቻለ የትምህርት ምዘና (IEE) የማግኘት መብት አለዎት።
3. በምዘናው ሂደት ለልጅዎ ለሚሰጠው ለእያንዳንዱ ፈተና ሁሉ አንድ IEE መጠየቅ የሚችሉ ይሆናል።
4. እባክዎን ሁሉንም የ IEE ጥያቄዎች በቀጥታ ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር እና/ወይም የተማሪ ድጋፍ አስተባባሪ ያቅርቡ።
5. ለ IEE ጥያቄ በሚቀርብ ጊዜ የትምህርት ቤቱ ክፍል ገለልተኛ ምዘና ለማግኘት እንዲሁም ለተደረገው ምዘና ማናቸውንም መስፈርቶች መረጃ ያቀርብልዎታል።
6. ተማሪው የአካል ጉዳት ያለበት እንደሆን ይህን ለማወቅ ትምህርት ቤቱ ለምዘና ስለሚጠቀም IEE የምዘናው ቦታ እንዲሁም የተፈታኙን መመዘኛዎች ጨምሮ ተመሳሳይ የሆኑ መስፈርቶች ማግኘት አለበት።
7. በአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (APS) የማያውቀው አቅራቢ በወላጅ በኩል የሚመረጥ ከሆነ በ IEE መሰረት ምዘና ከመደረጉ በፊት ተሟልቶ መገኘት ይኖርበታል። እነዚህ መስፈርቶች በዚህ ሰነድ ገጽ 4 ላይ ይገኛሉ።

እባክዎን ያስታውሱ APS ምዘና አድራጊው ተገቢነት እንዳለው ለማሳየት የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል። የፍርድ ቤቱ ሹም የትምህርት ቤቱ ምዘና ተገቢ ነው ብሎ የሚወስን ከሆነ አሁንም IEE የማግኘት መብት ያለዎት ሲሆን ነገር ግን ትምህርት ቤቱ ለዚህ ክፍያ አይከፍልም።

በተጨማሪ የ IEE ውጤቶችና በግለሰብ ደረጃ ወጪ በማድረግ የሚያገኟቸው ማንኛቸውም ምዘናዎች ከትምህርት ቤት ክፍል ጋር ስለሚካፈሉ ሲሆን የልጅዎን ልዩ ትምህርት በሚመለከት በማንኛውም ውሳኔ ላይ ከግምት የሚገቡና በእርስዎ ወይም በትምህርት ቤቱ ክፍል አማካኝነት በፍትህ ሂደት ችሎት ላይ እንደ ማስረጃ ሊቀርቡ ይችላሉ።

በመንግስት ወጪ ማካሄድ ማለት በፌደራልና በስቴት ደንቦች መሰረት LEA ለምዘናው ሙሉ ወጪ ክፍያን ይፈጽማል ወይም ምዘናው ያለ ምንም ወጪ ለወላጅ መሰጠቱን ያረጋግጣል።

የ IEE ጥያቄ ያለውን የ APS ምዘና ወላጆች እንዲያገኙ በተገቢው ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት። ምዘናዎቹ የተካሄዱት ከሁለት አመት በፊት ከሆነ የቅርብ ጊዜ እንዳልሆኑ ተደርገው የሚቆጠሩና ለ IEE ብቁ አይሆኑም። የ IEE ማካካሻዎች በጊዜው እንዲስተናገዱና እንዲታሰቡ ለማድርግ APS ተገቢ የሆነ እርምጃ ይወስዳል።

*መመሪያውን ማክበር ሊከሰቱ የሚችሉ መዘግየቶችን የሚያስቀርና የ IEE ጥያቄን በጊዜው ለማሄድ ያስችላል። እባኮትን የፌደራልና የስቴት ደንቦችን ማጣቀሻ ይመልከቱ፡*

*ገለልተኛ የትምህርት ምዘና* (8VAC20-81-170)

1. አጠቃላይ። (34 CFR 300.502(*ሀ*))
   - *ሀ.* የአካል ጉዳተኛ ልጅ ወላጅ (ጆች) የልጁን ገለልተኛ የትምህርት ምዘና የማግኘት መብት አላቸው።
   - *ለ.* የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ ለአካል ጉዳተኛ ልጅ ወላጅ(ጆች) ራሱን የቻለ ትምህርታዊ ምዘና ሲጠየቅ ራሱን የቻለ ትምህርታዊ ምዘና የት ሊገኝ እንደሚችል መረጃን እንዲሁም ለገለልተኛ ትምህርታዊ ምዘናዎች ተገቢ የሆኑ መስፈርቶች ያቀርባል።

2. በመንግስት ወጪ ምዘና ለማድረግ የሚያስችል የወላጅ መብት። (34 CFR 300.502 (*ለ*) እና (*ሠ*))
   - *ሀ.* ወላጅ(ጆች) በአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ በተገኘው የምዘና ክፍል የማይስማሙ ከሆነ ወላጅ(ጆች) በመንግስት ወጪ ገለልተኛ የሆነ የትምህርት ምዘና የማግኘት መብት አላቸው።
   - *ለ.* ወላጅ(ጆች) በመንግስት ወጪ ገለልተኛ ትምህርታዊ ምዘና የሚጠይቁ ከሆነ፣ የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ፣ ያለአላስፈላጊ መዘግየት የሚከተለውን ያደርጋል፡
     - (1) ምዘናው ተገቢ መሆኑን ለማሳየት የፍትህ ሂደት ችሎት ይጀምራል፣ ወይም
     - (2) የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ በፍትህ ሂደት ችሎት ላይ በወላጅ(ጆች) የተገኘው ምዘና የአካባቢውን የትምህርት ኤጀንሲ መመዘኛዎች መስፈርት የማያሟላ መሆኑን እስላከተመለከተ ድረስ ገለልተኛ የትምህርት ምዘና በመንግስት ወጪ መሰጠቱን ያረጋግጣል።
   - *ሐ.* የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ የፍትህ ሂደት ከጀመረና የመጨረሻ ውሳኔዎች የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ ምዘና ተገቢ እንደሆነ ካመላከተ ወላጅ(ጆች) አሁንም ገለልተኛ የሆነ የትምህርት ምዘና የማግኘት መብት ያላቸው ሲሆን ነገር ግን ይህ በመንግስት ወጪ የሚካሄድ አይደለም።
   - *መ.* ወላጅ(ጆች) ገለልተኛ ትምህርታዊ ምዘና እንዲደረግ የሚጠይቁ ከሆነ የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ ወላጅ ለምን በመንግስት ምዘናው ላይ ተቃውሞ እንዳነሳ ምክንያቶቹን ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም፣ የወላጅ(ጆች) ማብራሪያ ላያስፈልግ የሚችልና የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ ያለምክንያት ሊያዘገየው ወይም ገለልተኛውን ትምህርታዊ ምዘና በመንግስት ወጪ ለማቅረብ ወይም የመንግስት ምዘናውን ለመከላከል የፍትህ ሂደት ሊጀምር ይችላል።
   - *ሠ.* የመንግስት ትምህርት ኤጀንሲ ወላጅ ያልተስማማበትን ምዘና ባደረገ ቁጥር ወላጅ በመንግስት ወጪ አንድ ትምህርታዊ ምዘና ብቻ የማግኘት መብት አለው።

ረ. ገለልተኛ የትምህርት ምዘና በመንግስት ወጪ የሚካሄድ ከሆነ፣ የምዘናውን ቦታና የምዘና አድራጊውን መስፈርቶች ጨምሮ ምዘናው የተገኘበት መስፈርት የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ ምዘናን በሚጀምርበት ጊዜ ከሚጠቀምባቸው መመዘኛዎች ጋር ተመሳሳይ መሆን ያለበት ሲሆን እነዚህ መመዘኛዎች ከወላጆች ነጻ የትምህርት ምዘና የማግኘት መብት ጋር ተጣጥመው የሚሄዱ ናቸው። ከቀረቡ መመዘኛዎቹ በስተቀር የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ በመንግስት ወጪ ራሱን የቻለ የትምህርት ምዘና ከማግኘት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁኔታዎችን ወይም የጊዜ ገደቦችን በማስቀመጥ ሊያስገድድ አይችልም።

3. በወላጆች አነሻሽነት የሚደረጉ ምዘናዎች። ወላጅ ገለልተኛ ትምህርታዊ ምዘና በመንግስት ወጪ ካደረገ ወይም በግል ወጪ የተደረገውን ምዘና ለአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ ቢያጋራ፣ የምዘናው ውጤቶች፡ (34 CFR 300.502(ሐ))

ሀ. ለልጁ ተገቢ የሆነ ነጻ የመንግስት ትምህርት ማግኘቱን በሚመለከት በማንኛውም ውሳኔ የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ከሆነ በአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ ይሄ የሚያዝለት ይሆናል፣ እና

ለ. በ 8VAC20-81-210 ስር ባለው የፍትህ ሂደት ላይ በማንኛውም አካል እንደ ማስረጃ ሊቀርብ ይችላል።

4. በልዩ ትምህርት የፍትህ ሂደት መኮንኖች የቀረቡ የምዘና ጥያቄዎች፡ የልዩ ትምህርት ሰሚ መኮንኑ እንደ የፍትህ ሂደት ቅሬታ ችሎት አካል ለምዘና ክፍሉ ገለልተኛ ትምህርታዊ ምዘና እንዲካሄድ ጥያቄ ካቀረበ፣ የምዘናው ወጪ በመንግስት ወጪ የሚካሄድ ይሆናል። (34 CFR 300.502(መ))።

አርሊንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች
የልዩ ትመህርት ቢሮ
2110 Washington Blvd. 2nd Floor
Arlington, Virginia 22204
703-228-6040

የምዘና አድራጊው መመሪያዎች

እነዚህን ደንቦች መሰረት በማድረግ፣ የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (APS) የሚከተሉትን መመዘኛዎች አዘጋጅቷል፡

I. ምዘና አድራጊዎች የሚከተሉትን ለተገዢነት ልዩ ባለሙያ ወይም ለልዩ ትምህርት ዳይሬክተር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡

ሀ. በሜሪላንድ ወይም በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ከሆነ፣ ከቨርጂኒያ የትምህርት ቦርድ ወይም ተመሳሳይ ከሆነ አካል ትክክለኛና ወቅታዊ ፈቃድ መያዝ አለባቸው።

ለ. አቅራቢዎች የቅርብ ጊዜም ሆነ ቀድሞ የነበረ ምንም አይነት ጥሰት ያልፈጸሙና በዙሪያው ባሉ ስቴቶች ውስጥ በመልካም አፈጻተም ላይ የሚገኙ መሆን አለባቸው።

ሐ. ምዘና ለተደረገለት ተማሪ ተመሳሳይ ፍላጎት ካላቸው ተማሪዎች ጋር፣ ሁለቱም የምዘና የእድገት ደረጃዎች እንዲሁም ትምህርታዊ ጉዳዮች ላይ APS ያላቸውን ልምድ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ቀደም ሲል በተጻፉ ምዘናዎች መልክ ማስረጃዎችን ማቅረብ የሚቻል ይሆናል።

II. ምዘናው በሚደረግ ጊዜ የሚከተሉት ደረጃዎችና መመሪያዎች መከበር ይኖርባቸዋል፡

ሀ. ተማሪውን ምዘና ከመደረጉ በፊት፣ ምዘናውን የሚያካሂዱት ከላይ የተገለጹት መመዘኛዎች እንደቀረቡ፣ እንደተገመገመና IEE ለማካሄድ በ APS የተፈቀደላቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ የጽሁፍ ማረጋገጫ የሚደርሳቸው ይሆናል።

ለ. ምዘናውን የሚካሄደው ጽህፈት ቤት፣ የትምህርት ተቋም ወይም በሌላ ተገቢ በሆነ ሙያዊ ሁኔታ ውስጥ ነው። የተሟላ የምዘናው ውጤት የሚሰጠው ትምህርት ቤቱ ክፍል ፈቃድ ባገኘ ግለሰብ ብቻ ነው።

ሐ. ሁሉም ፈተናዎች በግል መሰጠት ይኖርባቸዋል።

መ. በቅርብ የተወሰደው ፈተና ብቻ ያገለግላል።

ሠ. ሁሉም ፈተናዎች በፈተና መመሪያው ውስጥ በተሰጠው መመሪያ መሰረት የሚሰጥና ውጤቱ የሚያዝ ይሆናል።

ረ. በተለየ ሁኔታ ቅድመ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ በስተቀር ፈተናዎች ሙሉ በሙሉ መሰጠት አለባቸው።

ሰ. ልኬት ወይም ጥቅል (ክላስተር) ያካተቱ ሁሉም ፈተናዎች ወይም ንኡስ ፈተናዎች መሰጠት ያአለባቸው ሲሆን የልኬት ወይም የጥቅል (ክላስተር) መደበኛ ውጤቶች ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

ሸ. ፈተናዎች የሚመረጡት እያንዳንዱ ተለይቶ የሚታወቅ አሳሳቢ ቦታ መመዘኑን ለማረጋገጥ ነው። በ APS ሰራተኞች ለመጠቀም የተፈቀደላቸው የፈተናዎች ዝርዝር ጥያቄ በማቅረብ ማግኘት ይቻላል።

ቀ. የሚመረጡት ፈተናዎች በሙሉ ምዘናው ለሚደረግለት ልጅ በባህልና በቋንቋ ረገድ ተስማሚ መሆን ያለባቸውና ለሚጠቀሙበት የተለየ አላማ መገምገም አለበት።

በ. ውስን የእንግሊዝኛ ችሎታ ያለው ልጅ ምዘና እንዲደረግለት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችና ሂደቶች የልጁን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ከመለካት ይልቅ የአካል ጉዳት እንዳለበትና ልዩ ትምህርት የሚፈልገውን መጠን ለመለካት እንዲቻል ተመርጠው መሰጠት ይኖርባቸዋል።

ተ. ግልጽ በሆነ ሁኔታ የማይቻል ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ፈተናዎች በልጁ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም በሌላ የመግባቢያ ዘዴ መቅረብና መሰጠት አለበት።

ቸ. ፈተናዎች መምረጥና መሰጠት ያለባቸው ውጤቶቹ የልጁን ብቃት ወይም የውጤት ደረጃ በትክክል የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን ወይም ፈተናዎቹ የሚለኩባቸውን የልጁን የስሜት ህዋሳት፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ወይም የመግባቢያ ችሎታዎች ከማሳየት ይልቅ ለመለካት ያሰቡትን ሌሎች ነገሮች በትክክል ማንጸባረቅ እንዲችሉ ነው። ለዚህ ብቸኛው ልዩ የሚያደርገው ችሎታዎቹ በሚኖሩባቸው እነዚያ ነገሮች ላይ ፈተናው ለመለካት ያለማቸው ምክንያቶች ናቸው።

ኀ. መደበኛ ያልሆነ እና/ወይም መደበኛ ያልሆኑ እርምጃዎች መደበኛውን ፈተና እንዲሟላ ለማድረግ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

III. የምዘና ሪፖርቶችን በተመለከተ የሚከተሉት ደረጃዎችና መመሪያዎች መከበር ይኖርባቸዋል፡

ሀ. ተዛማጅነት ያላቸው የባህሪ ምልከታዎች በሪፖርቱ ውስጥ መገለጽ ይኖርባቸዋል።

ለ. ምዘናው በመደበኛ ሁኔታዎች ውስጥ የማይካሄድ ከሆነ ከመደበኛ ሁኔታዎች ምን ያህል እንደሚለያይ የሚገልጽ መግለጫ በምዘና ሪፖርቱ ውስጥ መካተት ይኖርበታል።

ሐ. ከተሰጡ ፈተናዎች የሚገኙ ውጤቶች አባሪ በሙሉ ከሪፖርቱ ጋር መቅረብ ይኖርበታል። ተቀባይነት ያለው መግለጫ ማካተት ያለበት ሲሆን ይህም ፈተናዎች በባህልና ቋንቋ ሁኔታዎች ላይ ተመርኩዘው እንዲሁም ውጤቶቹ ልክ እንደሆኑ በሚያረጋግጥ መልኩ የተዘጋጀ ሪፖርት መቅረብ አለበት።

መ. የግለሰብ ምዘና አድራጊዎች ያገኙትን ነገር ሪፖርት ለማድረግ ግባቸውን እንዲከተሉ ይጠበቅባቸዋል። በስቴት ያሉ ደንቦች እነዚህ ውሳኔዎች የሚደረጉት በባለብዙ የትምህርት መስክ ኮሚቴ ስለሆነ ምዘና አድራጊው ለምደባ ወይም ብቁ ለመሆን ልዩ ምክሮችን ከመለገስ መቆጠብ ይኖርበታል፡

VI. ወጪዎችና ክፍያ የሚፈጸምባቸው መጠኖች በ IEE ምዘና አይነት ላይ መሰረት በማድረግ የሚታሰቡ ይሆናል።

ሀ. እባክዎን የሂሳብ አከፋፈልና ክፍያን በማስመልከት ተመጣጣኝ ዋጋን በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የልዩ ትምህርት የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ዳይሬክተር ወይም የልዩ ትምህርት ተገዢነት ልዩ ባለሙያን በ 703-228-6040 ላይ ያግኙ።

ለ. ዋናው የ APS IEE ምዘና ሪፖርት ለወላጅ፣ አንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር ወይም የልዩ ትምህርት ተገዢነት ባለሙያ የሚቀርብ ይሆናል።

ሐ. የክፍያ መጠየቂያው፣ W-9 እና APS ስታርስ የአቅራቢ ማመልከቻ ለልዩ ትምህርት የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ዳይሬክተር ወይም ለልዩ ትምህርት ተገዢነት ልዩ ባለሙያ በኢሜል ወይም በአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በዩኤስ ፖስታ በፖስታ 2110 Washington Blvd. 2nd Floor, Arlington VA 22204 መቅረብ ይኖርበታል።

መ. እነዚህን መመሪያዎች አስመልክቶ ጥያቄዎች የሚኖርዎ ከሆነ እባክዎን የልዩ ትምህርት አንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ዳይሬክተርን ወይም ተገዢነትን ልዩ ባለሙያን በስልክ ቁጥር 703-228-6040 ያግኙ።